# በውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት የሚገነባ

# ዴሞክራሲ አለን ?

## ሃይሌ አረጋዊ 01/05/14

መቼም በዚህች ምድር ላይ ሰው ሆኖ ተፈጥሮ ከስህተት የፀዳ የለም፤ አምላክ ሳይሆን በሰው አምሳል የተፈጠረ ደግሞ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ሳያውቀው ስህተት ይፈጥራል፡፡ ለበጎ አልሞ ሲንቀሳቀስ ያልጠበቀው መጥፎ ውጤት ሊከሰትበት ይችላል፡፡ ይህኑና ስህተቱን እያረመ ከዛሬው ስህተት ለነገ ትምህርት የሚሆነውን እየቀሰመ፣ እያሻሻለ ይሄዳል፤ ከዛሬው ተግባሩ ለነገ ፣ ከዘንድሮው ምግባሩ ለሚቀጥለው አመት የሚሆነውን ትምህርት እየቀሰመ ውሎ ሲያድር እየተሻሻለ መሄድ በሰው ልጆች ውስጥ ታሪክ ውስጥ ያለና የነበረ ወደፊትም የሚኖር ነው፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ መልኩ ከትናንት ስህተቱ ለዛሬ የሚሆነውን ትምህርት የማይቀስመውን ከአምና ዘንድሮ መሻሻል የማያሳየውን ግን የአገሬ ሰው "አድሮ ቃሪያ ፣ ቢወቅጡት እምቦጭ" የሚሉ እና የመሳሰሉትን ስያሜ ይሰጠዋል፡፡ ይህ አባባልም ስህተት መስራት ምንም ነውር እንደሌለው ከስህተት አለመማር ግን ጅላጅልነትና አላዋቂነት መሆኑን በመግለፅ ማህበረሰቡን ለማስተማር በማሰብ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ዛሬ ላይ የደረሰ ትውፊት ነው፡፡

ይህን እንድል ያነሳሳኝ ታድያ መድረክ በመባል የሚታወቀው ተቃዋሚ ፓርቲ ጉሙቱ አመራሮች መካከል አንዱ የሆኑት ባለፈው ሰሞን ወይዘሮ አና ጎሜዝ በአዲስ አበባ ቆይታ ባደረጉበት ወቅት አግኝተዋቸው " በኢትዮጵያ ኢህአዴግ ያጠበበው የፖለቲካ ምህዳር እንዲሰፋ ፣ ዴሞክራሲው እንዲጎለብትና የመሳሳሉት ተግባራዊ እንዲሆን ከእኛ ተቃዋሚዎች ምን ይጠበቃል" የሚል ጥያቄ ማቅረባቸውን ከአንድ የግል ጋዜጣ በማንበቤ ነው፡፡

ሴትዮዋም የቀለም አብዮት ጠበብት ናቸውና ከዚህ ጥልቅ ሙያቸው ተነስተው ለእኝሁ ጥያቄ አቅራቢ የመድረክ አመራር ፍቱን መድሃኒት ናቸው ያላቸውን የመፍትሂ ሃሳቦች አንድ ሁለት ብለው ጠቋቁመዋል፡፡

የቀለም አብዮት ጠበብቷ ወይዘሮ አና ጎሜዝ በዚሁ ምላሻቸው በደካማ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ በመጥቀስ የተበሳጩባቸውን የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች መጪው ምርጫ እየተቃረበ በመሆኑ እርስ በእርሳቸውም በውጭም ካሉ እርሳቸውን ከመሰሉ ሃይሎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር በገዥው ፓርቲና በመንግስት ላይ ጫና እንዲፈጥሩ በጥብቅ ማሳሰባቸውን ጋዜጣው ገልጿል፡፡

በወይዘሮ አና ጎሜዝና በጉምቱው የመድረክ አመራር መካከል የተካሄደውን ይህን በኢትዮጵያ ጉዳይ የውጭ ጣልቃ ገብነትን የሚጋብዝ የሁለትዮሽ ምክክር በዚሁ ጋዜጣ ላይ ካነበብኩ ከጥቂት ቀናት በሁዋላ ደግሞ እነዚሁ የመድረኮቹ አመራር በአዲስ አበባ ከሚገኙ የተለያዩ የምእራባውያን ኤምባሲ ዲፕሎማቶችና አምባሳደሮች ጋር በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ዙሪያ ውይይት ማካሄዳቸውን ሰማሁ፡፡

የመድረኩ ጉምቱ ባለስልጣናት በዚሁ ከዲፕሎማቶች ጋር ባካሄዱት ውይይትም "በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ የፖለቲካ ምህዳሩ እየጠበበ መምጣቱን ፣ መንግስት የዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማፈን መቀጠሉንና የመሳሰሉትን ክስ መድረደራቸውን" ከታማኝ ምንጮች መረዳት ችያለሁ፡፡

ይህ ግርምቴ ነው ቀደም ሲል እንደገለፀኩት በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተሰማኝን ለማለት ብእሬን እንዳነሳ ያስገደደኝ፡፡እንደሚታወቀው የመድረክ አመራሮች ባለፉት ሃያ አንድ አመታት ምርጫ በመጣ ቁጥር በአዲስ አበባ ባሉ የምእራባውያን ኤምባሲዎች ጎራ ማለትን እንደልማድ ካደረጉት አመታት አስቆጥረዋል፡፡

ታድያ እነዚህ አመራሮች ወደ ኤምባሲዎች ጎራ ባሉ ቁጥር በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታው ይበልጥ እንዲጎለብት የምእራብ አገራት መንግስታት በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና እንዲያደርጉ ነው የሚወተውቱት፡፡

እዚህ ላይ ግን ድፈረት ካልሆነብኝ ምሁራን ነን ለሚሉት ጉሙቱ የመድረክ ባለስልጣናት አንድ ጥያቄ ማቅረብ ፈልግኩ፤

ለመሆኑ የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ይበልጥ የሚጎለብተው በኢትዮጵያውያን በራሳቸው አሊያስ በውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት? ድፍረት ባይሆንብኝ ያልኩት የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ይበልጥ የሚጎለብተው በመላው የኢትዮጵያውን ህዝቦችና ብሄር ብሄረሰቦች ተሳትፎ መሆኑን ማንም ፊደል ያልቆጠረ ኢትዮጵያዊ ሴኮንድ ሳይፈጅበት ምላሽ የሚሰጥበት ርእሰ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ለእናንተ ከፍተኛ ምሁራን ነን ባይ የትርፍ ስአት ፖለቲከኞች የሆናችሁ የመድረክ አመራሮች ይህን ለማስረዳት የደፈርኩት በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደት ላይ ወይዘሮ አና ጎሜዝንና በአዲስ አበባ የሚገኙ የምእራብ አገራት ዲፕሎማቶችና አምባሳደሮችን ምክር የመጠየቃችሁን ዜና ስሰማ የፖለቲካ ግንዛቤያችሁ ያለበት ደረጃ እጅግ ስላስደነገጠኝ በመሆኑ እንደሆነ እንድትገነዘቡልኝ እፈልጋለሁ፡፡

እዚህ ጋር በዚህ አጋጣሚ አንባቤዎቼ እንድትገነዘቡልኝ የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር የመድረክ አመራሮች በማንኛውም ጊዜና ወቅት በየትኛውም አለም ከሚገኙና የትኛውንም አይዲዎሎጂ ከሚያራምዱ ሃይላት ጋር በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የውጭ ጣልቃ ገብነትን በማይጋብዝ ጉዳይ ላይ ከሆነ ውይይት የማድረግ ህገ መንግስታዊ መብት እንዳላቸው የምገነዘብ መሆኔን ነው፡፡

ይሁን እንጂ እያወገዝኩ ያለሁት ምርጫ በመጣ ቁጥር የአሁኑን ጨምሮ ባለፉት አገር አቀፍ ምርጫ ዋዜማዎች ማለትም በ1997 እና በ2002 አም እንደታዘብነው የመድረክ አመራሮች በምእራባውያን ኤምባሲና በውጭ አገራት እየተዘዋወሩ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ የውጭ ሃይላት ጣልቃ እንዲገቡ መወትወታቸውን ነው፡፡

በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ጉዳይ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጉዳይ ብቻ በመሆኑ የማንንም የውጭ ሃይል ጣልቃ የሚያስተናግድበት ቦታ የሌለው ከመሆኑ አንፃር መድረኮች ይህን ያልተገባ እንቅስቃሴቸውን ቆም ብለው ቢፈትሹት የተሻለ ይመስለኛል፡፡

በእርግጥ እነዚህ ሃይሎች ምርጫ በመጣ ቁጥር በየኤምባሲው ደጃፍ የሚኳትኑትም ሆነ ፈረንጅን ደጅ የሚጠኑት ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያቀርቡለት አንድም አይነት የፖሊሲና የስትራቴጂ አማራጭ ስለሌላቸው እንደሆነ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ነው፡፡

እነዚህ ሃይሎች ለኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ ፖሊሲና ስትራቴጂ ይዘው ሊቀርቡ ቀርቶ እንዴያውም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቃቸው በአገሪቱ የሚካሄዱ የተለያዩ የልማት ፕሮጄክቶችን የተለያዩ ሰበብ አስባቦችን በመፍጠር ሲቃወሙ ነው (የህዳሴውን ግድብ ፣ የባቡር ሃዲድ ግንባታና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

እነዚህ ሃይሎች መላ አገሪቱን እጅግ ፈጣን በሆነ ኢኮኖሚያዊ እድገት በመምራት ላይ የሚገኘውን መንግስት ማንኛውም ተግባራት ተግተው ለመቃወም ከማሰፍሰፋቸው ጋር ተያይዞ በገጠር የግብርና ልማቱን በጠነከረ መሰረት ላይ ለማቆም የሚካሄደውን የሠፈራና ጥቅም ላይ ሳይውል የቆየ ባዶ መሬት እንዲለማ ለባለሃብቶች የመስጠት ተግባር ያለማቋረጥ ሲቃወሙ ይሰማሉ፣ በከተሞች የሚታየውን የስራ አጥነትን ለመቅረፍ የሚያስችል የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ሲያስፋፉና የትምህርት አገልግሎት ለዜጎች ለማዳረስ የሚያካሂደውን ተግባርም ሲያቃወሙ ይስተዋላሉ፡፡

በመሆኑም መድረክ በሚል የተሰባሰቡት እነዚህ ሃይሎች ባለፉት ጊዜያት በተደጋጋሚ የጠሯቸው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በጣት የሚቆጠር ሰው ብቻ ሲገኝና የስብሰባዎቻቸው አዳራሾችም ባዶ ሲቀሩ በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ ማንነታቸውን ገበናቸው ይበልጥ እንደተጋለጠ ግልፅ አድርጎላቸዋል፡፡

ይህም ቀድሞውንም ጊዜ እየጠበቁ ምርጫ በመጣ ቁጥር የማይጠፉባቸው የውጭ ኤምባሲዎች ደጆች በመኮልኮል ጣልቃ ግቡልን ወደሚለው የቀድሞ ዜማቸው እንዲመለሱ አስገድዷቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ በተደጋጋሚ እንደሚገለፀው የኢትዮጵያ መንግስት በታሪኩ አንድም ጊዜ ቢሆን ለውጭ ሃይሎች የተንበረከከበት አሊያም "ይህን አድርግ ይህን አታድርግ" ለሚል የውጭ ሃይል ትእዛዝ ራሱን አሳልፎ የሰጠበት አንድም የታሪክ አጋጣሚ የለውም፡፡

ይህን በውል መገንዘብ የተሳናቸው "መድረክ" የተሰኘው ሃይል አመራሮች ግን አድሮ ቃሪያ እንደሚለው የአገሬ ሰው ዛሬም ከትናንቱ ትምህርት ሳይቀስሙ የምእራባውያን

መንግስት በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ላይ ጣልቃ እንዲገባ በመወትወት ላይ ይገኛሉ፡፡

ዛሬ ጊዜው ገና ነው ፤ የ2007 ምርጫ ሊደርስ የአንድ አመት ጊዜ ያህል ቀርቶታል፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በምርጫ ድምፁን እንዲሰጠው የፈለገ ማንኛውም ሃይል የኢትዮጵያን ፈጣን ልማት ይበልጥ የሚያስቀጥል የተጀመረውን የዴሞክራሲ ስርአ ግንባታ ይበልጥ የሚያጎለብት አማራጭ ፖሊሲና ስትራቴጂ ብቻ ይዞ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡

በመሆኑም ዛሬ በኢትዮጵያ ስልጣን በአቋራጭ በውጭ ሃይል አንጋሽነት የማይገኝበት ሁኔታ መፈጠሩን የመድረክ አመራሮች ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት መቼም ቢሆን ለውጭ ሃይል ተንበርክከው ከአቋማቸው ሸብረክ ያሉበት ጊዜ በታሪክ የታየበት ሁኔታ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ “ የመድረክ አመራሮች በአሁኑ ወቅት ወይዘሮ አና ጎሜዝንም ሆነ በየኤምባሲው የሚገኙ ዲፕሎማቶችን “በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ስርአት እንዲሰፍን ምን ማድረግ ይገባናል” እያሉ መጠየቃቸው የኢትዮጵያን ህዝብ በአግባቡ አለመረዳታቸውን በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡

በተለይ የመድረክ አመራሮች ለወይዘሮ አና ጎሜዝ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ያቀረቡት ጥያቄ “እውርን እውር በሚራው ......ተያይዞ ገደል” የሚለውን እንዳስታውስ አደርጎኛል፡፡

እነዚህ የመድረክ አመራሮች ለውጭ ሃይሎች በየጊዜው የሚያቀርቡት ይህ የውጭ ጣልቃ ገብነትን ናፋቂነት ጥያቄ የአገሩን የውስጥ ፖለቲካና ልኡላዊነትን ሊዳፈር የመጣን የውጭ ጠላት አሳፍሮ በመመለስ የሚታወቀውን ኩሩውን የኢትዮጵያ ህዝብ በተንሸዋረረ እይታ ከማየታቸው የመነጨና ካለፈው ስህተታቸው ትምህርት አለመውሰዳቸውን ዳግም ያረጋገጠ በመሆኑ “ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ” የሚለው ስያሜ ለእነዚህ አመራሮች ገላጭ አባባል ይመስለኛል፡፡

በውጭ ሃይሎች ታግዞ የስልጣን ማማ ላይ ለመቆናጠጥ የሚያስችል እድል በኢትዮጵያ ምድር ላይ ቢኖር ኖሮ በ1997 ዓ.ም እነዚህ ሃይሎች ቅንጅት በሚል ስም ተሰባስበው ያደረጉት ሙከራ በተሳካ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ይህ አይነት በውጭ ጣልቃ ገብነት የሚገኝ ስልጣን እንደማይሳካ በ2002 አም በተወሰነ መልክ ተደርጎ የነበረው ሙከራችሁ አመላካች መሆኑን ልጠቅስ እወዳለሁ፡፡

የውጭ ሃይሎች አዛዥና ጌትነታቸው ለመድረክ አመራሮች ብቻ እንጅ ለኢትዮጵያ ህዝብም ባለመሆኑም የመድረክ አመራሮች ዛሬም "አይኔን ግንባር ያድርገው" የሚለውን ስትራቴጂ እንደ ስልት በመጠቀም ባረጀና ባፈጀ አመለካከታቸው መቀጠላቸው በኢትዮጵያ በፍጥነት በመለወጥ ላይ ካለው ሂደት ጋር እራሳቸውን አጣጥመው መሄድ እንደማይችሉ ዳግም ያረጋገጠ ነው፡፡

እነዚህ ያረጀ አመለካከት ባለቤቶች በኢትዮጵያ ባለፉት የምርጫ ጊዜያቶች እንዳደረጉት ሁሉ ዛሬም በሚመኙት የስልጣን ኮረቻ ላይ የመቆናጠጥ ህልማቸውን እውን ለማድረግ የኢትዮጵያ መንግስት በውጭ ሃይል ጫና እንዲደረግበት መማፀናቸው ባለበት የቆመው አስተሳሰባቸው አሁንም አንዳች ለውጥ እንዳላመጣ ያመላከተ ነው፡፡

ሆኖም ግን በአገራችን እየተገነባ ያለው የዴሞክራሲያዊ ስርአት ሂደት ይበልጥ የሚጎለብተው የስልጣን ባለቤት በሆነው ህዝቡ ተሳትፎ ብቻ መሆኑን ዛሬም እነ መድረክ እንዲገነዘቡት መጠቆም የግድ ይላል፡፡

ምክንያቱም እነ መድረክ እንደ ጌታ የሚቆጥሯቸው የውጭ ሃይሎች ጌትነታቸው ለእነርሱ ብቻ እንጂ ለኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት እንዳልሆነ ተገንዝበው የውጭ ሃይሎችን በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዲገቡ ከመወትወት ሊቆጠቡ በተገባ ነበርና፡፡

ሆኖም ግን ካለፈው ስህተት መማር ያልቻሉት የመድረክ አመራሮች ይህንኑ አጠናክረው ቀጥለውበታል፡፡ሆኖም ግን የመድረክ አመራሮች ከስህተታችሁ ለመማር ከፈለጋችሁ ዛሬም ቢሆን አልረፈደምና በፈጣን እድገትና ለውጥ ላይ የምትገኘዋን ኢትዮጵያችንን ለመምራትና ለማስተዳደር ብቸኛው አማራጭ ይህንን ለማስቀጠል የሚያስችል የስትራጂካዊ አመራር አማራጭ ይዞ መገኘት ብቻ መሆኑን ልብ ብትሉት ይጠቅማል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ባለ ያለማንም የውጭ ጣልቃ ገብነት የዴሞክራሲ ሂደቱን በህዝቦቹ ተሳትፎ ብቻ እያጠናከረና እያጎለበተ በሚሄድ አገር ላይ ላይ አሁንም አማራጭን አስተካክሎ፣ የቆዩበትን አካሄድ ፈትሾና ገምግሞና ብቁ የምርጫ ተወዳዳሪዎችን አዘጋጅቶ ዳግም በውድድሩ ሜዳ ላይ ተሳታፊ መሆን ከማንኛውም የዴሞክራሲው ሂደት አካል የሚፈለግ በመሆኑ በዚሁ እንድትገፉበት ምክሬን ልለግሳችሁ እሻለሁ ፡፡

በኢትዮጵያ ዛሬም እንደ ትናንቱ የስልጣን እርከን ላይ መውጣት የሚቻለው በሰላማዊውና ህጋዊው ምርጫ ተወዳድሮና ተፎካክሮ በሚገኝ የህዝብ ድምፅ ብቻ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ፡፡ከሰላማዊ ምርጫ ውጭ በኢትዮጵያ ሌሎች አማራጮች በሙሉ ዝግ መሆናቸውን አሁንም ልብ ሊባል ያስፈልጋል፡፡

ምናልባትም የመድረክ አመራሮች ነገም ሌላ ቀን ነውና ትምህርት ለመቅሰም ጆሮአችሁን የምትሰጡኝ ከሆነ በኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ በሚካሄድ ምርጫ የኢትዮጵያውያንን የምርጫ ድምፅ አግኝቶ ለስልጣን ለመብቃት የሚያስችለውን አማራጭ ፖሊሲና ስትራቴጂ ለመቅረፅ ዛሬም ጊዜው አልረፈደም ባይ ነኝ፡፡

ሆኖም ግን መድረክ የተባለው ሃይልና ስብስቡ ይህኛውን ሰላማዊ አማራጭ ትቶ አሁንም የውጭ ሃይል ጣልቃ ገብነት ስናፍቅ እኖራለሁ ካለ ግን “አርባ አመት ውቅያኖስ ውስጥ የኖረ ድንጋይ ተዘፈዘፈ እንጂ መች ዋና ተማረ” የሚለውን ተረት ላስታውሳቸው እወዳለሁ፡፡

ቸር ይግጠመን !